# ጸራቤ መናፍቃን (ዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ)

## የቅዱሳን ምልጃ በመጽሐፍ ቅዱስ

አሰቀድሜ የፕሮቴስታንት እምነት እንደአጠቃላይ እንዴት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንደሚጋጭ አሳይቼ ነበር። በእግዚአብሔር ረዳትነት ያንን ያሳየሁት መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ ወደ ቅዱሳን አባቶች ሊቃውንት እንደሚመራን በማሳየት ነው። እርሱን በ"የአባቶችን ትርጓሜ ለምንድን ነው መረዳት የሚያስፈልገው?" በሚለው ጽሑፍ ላይ ዳሥሻለሁኝ። አሁን ደግሞ ሌላ እጅግ በቀላሉ አንድ ፕሮቴስታንትን ከእምነቱ ነቅንቆ ለማስወጣት የምንጠቀምበት መንገድ ነው። ይህም የቅዱሳን ምልጃ (Communion of Saints) ነው። ይህ ትምህርት ፕሮቴስታንቶች በኅብረት የሚቃወሙት ትምህርት ሲኾን በመጽሐፍ ቅዱስ ግን በግልጥ የተቀመጠ የጌታችን ትምህርት ነው። ይህንን ደግሞ አሁን ከመጽሐፍ ቅዱስ እናብራራለን።

ፕሬቴስታንቶች ኦርቶዶክሳውያንን ከሚወቅሱባቸው ነገሮች መካከል "ኦርቶዶክሳውያን ሰዎችን ፍጡራንን የሚያመልኩ የጣዖት አምላኪዎች ናቸው።"፣ "የማርያም (ላቲ ስብሐት)፣ የተክለ ሃይማኖት፣ የመላእክት አምላኪዎች ናቸው።"፣ "በቀጥታ ከክርስቶሰ ጋር መገናኘት የማይፈልጉ ናቸው።"፣ "የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለድኅነት አይደለም ፥ ገና የቅዱሳን ምልጃ ያስፈልጋል የሚሉ ከሓድያን ናቸው።" የሚሉ የተወሰኑት ናቸው። አንድ ኦርቶዶክስ ይህንን ሲመልስ መሄድ ያለበት መንገድ ይህንን ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ወደማረጋገጥ ነው እንጂ የትኛውንም ዐይነት ግልባጭ መልስ አያስፈልገውም። አሁን ይህንን ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሳረጋግጥ ፕሮቴስታንቱ የፈለገውን ቢል ሐዋርያቱን እያላቸው እንደኾነ ይወቅ። "ጣዖት አምላኪ ነህ" ሲለኝ በሌላ አነጋገር "ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ቅዱስ ጳውሎስ በሙሉ የጣዖት አምላኪዎች ናቸው፣ እንዲያውም ጌታችን ራሱ ጣዖት አምላኪ ነው።" እያለ ይኾናል ማለት ነው። መቼም አንድ ፕሮቴስታንት ይህንን መንገድ መከተል አይፈልግም ፥ ስለዚህ ምላሱን መቆጠብ ይኾናል ሥራው ማለት ነው።

በዚሁ እንደማስታወሻ መያዝ የሚገባችሁ ነገር ፕሮቴስታንት የሚለው ቃል በውስጡ ብዙ ዐይነት እምቶችን ያካተተ ጠቅላይ ስም ነው። በፕሮቴስታንት እምነት ውስጥ የተለያዩ ቅርንጫፎች ይገኛሉ። ለምሳሌ ያህል ፥ Evangelical, Church of Christ, Anglican, Lutheran, Pentecostal, Calvinist, etc… የሚባሉ ቅርንጫፎች አሉት። በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም በዋነኝነት የሚገኙት Pentecostal ወይም በዐማርኛ ጴንጤ እየተባሉ የሚጠሩት የፕሮቴስታንቲዝም ቅርንጫፍ ናቸው። የተለያዩ የቅርጫፍ አማኞችን ስታገኙ ተቃራኒ የሚኾኑ እምነቶችን ልታገኙ ትችላላችሁ። በነገረ ቅዱሳን ላይ ግን አብዛኞቹ ስለሚስማሙ ከየትኛውም ፕሮቴስታንት ጋር ብትወያዩ የተለያየ ሐሳብ አታገኙም። አሁን ወደ ነገራችን እንመለስ ፥ ስለዚህ የቅዱሳንን ምልጃ ለማረጋገጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ነገሮች ማረጋገጥ በቂ ነው።

1) አንድ ክርስቲያን ለሌላ ክርስቲያን እንዲጸልይ ታዟል።
2) የቅዱሳን ጸሎት ደግሞ ለእግዚአብሔር በጣም ቅርብ ነው ፥ ስለዚህ የበለጠ ኀይል አለው።
3) ቅዱሳን ካረፉ በኋላ በገነት ውስጥ ንጹሓን፣ ከኀጢአት የተላቀቁ ይኾናሉ።
4) ቅዱሳን በሰማይ በገነት ህያዋን ናቸው። (የሞቱ አይደሉም)
5) እግዚአብሔር ለቅዱሳን በምድር የሚከናወነውን እንዲያውቁ አድርጓቸዋል።

አንድ ክርስቲያን ለሌላ ክርስቲያን እንዲጸልይ ታዟል ፥ ስለዚህ ቅዱሳን ለሌሎች መጸለይ ይችላሉ ማለት ነው። ከዚያ ደግሞ በተለየ ቅዱሳን ደግሞ ከኀጢአተኞች የበለጠ ክብር ስለተሰጣቸው ጸሎታቸው ከኀጢአተኞች በእግዚአብሔር ፊት ደስ የሚያሰኝ ፥ መልስም ለማሰጠት ፈጣን ነው ማለት ነው። ስለዚህ እኛ ጸሎትን ሳንተው ለቅዱሳን ጸልዩልን ብንላቸው ለጸሎታችን የበለጠ ፈጣን መልስ እናገኛለን ማለት ነው። ከዚያ ደግሞ ቅዱሳን በሥጋ ከተለዩን በኋላም ህያዋን ከኾኑ በምድር ላይ ደግሞ የሚኾነውን በእግዚአብሔር ኀይል የሚያውቁ ከኾነ እንዲያውም ከኀጢአት የተላቀቁ ንጹሓን ከኾኑ እኛ አሁንም ጸልዩልን ብንላቸው ይሰሙናል ፥ እንዲያውም በምድር ሳሉ ከኀጢአት ጋር ሲታገሉ ካሉበት ሁኔታ የበለጠ በሰማይ ጸሎታቸው ይሰማል። ስለዚህ የቅዱሳን ምልጃ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደኾነ አረጋገጥሁኝ ማለት ነው። ስለዚህ አንድ ፕሮቴስታንት ካነሣኋቸው ሐሳቦች መካከል የትኛው ልክ እንዳልኾነ ማሳየት እስካልቻለ ድረስ ይህ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐዋርያዊ ትምህርት ኾኖ ይቀጥላል ማለተ ነው። ይህንን ከፈጸምን በኋላ ደግሞ ይህ ትምህርት ሐዋርያዊ እና ታሪካዊ ትምህርት እንደኾነ ከቅዱሳን አባቶች ሊቃውንት እናሳያለን። ልክ ይህ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ሐዋርያዊ ትምህርት እንደኾነ ካሳየን ፥ ያን ጊዜ የፕሮቴስታንቲዝም ዐምድ ይመታል ፥ የፕሮቴስታንት እምነትም በራሱ ላይ ተገልብጦ ይፈርሳል። ስለዚህ እኒህን 5 ነጥቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ ወደ ማረጋገጥ እሄዳለሁኝ።

### ፩. አንድ ክርስቲያን ለሌላ ክርስቲያን እንዲጸልይ ታዟል።

# ጸራቤ መናፍቃን (ዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ)

ይህ የሚያጣላ ርእስ አይመስለኝም ፥ ነገር ግን ምናልባት ጠርጣራ ከተገኘ ከመጽሐጽ ቅዱስ ወደማረጋገጥ እቀጥላለሁኝ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ብዙ ቦታ አማኞች አንዱ ለሌላው እንዲጸልዩ ተነግሯል። ይህንን ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከጥግ እስከ ጥግ ተገልጾ ይገኛል። ስለዚህ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንሂድ፥

/**መዝ** 123 ፥ 6-9/

“6 ለኢየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ፤ አንተንም ለሚወድዱ ልማት ይሁን።

7 በኃይልህ ሰላም፥ በጌጠኛ ቤትህም ልማት ይሁን።

8 ስለ ወንድሞቼ ስለ ባልንጀሮቼም፦ በውስጥሽ ሰላም ይሁን አልሁ።

9 ስለ አምላካችን ስለ እግዚአብሔር ቤት ላንቺ መልካምነትሽን ፈለግሁ።“

- ቅዱስ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ የተናገረውን ቃል አድምጥ ፥ ለሁሉም አማኞች ትእዛዝን አዘዛቸው። “ለኢየሩሳሌም ለምኑ” ብሎ ፥ ‘ለኢየሩሳሌም’ ያለው ስለማን ነው ብለው ቢጠይቁት ደግሞ ከሥር ያብራራዋል። “ስለወንድሞቼ ስለ ባለንጀሮቼም ፥ በውስጥሽ ሰላም ይሁን አልሁ።“ ብሎ እያወራ ያለው ስለድንጋዩ እና ስለግብታው አይደለም። ይልቁንም ለምኑ፣ ጸልዩ እያለ ያለው ስለህዝቧ ነው። ለሌላው መጸለይ ገና ከጥንትም የነበረ ትምህርት ነው ማለት ነው። ነገሩ ግን ገና እያማረ ይመጣል።

/**ሮሜ** 10 ፥ 1/

“1 ወንድሞች ሆይ፥ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው።“

/2**ኛ ቆሮ** 13 ፥ 7/

“7 ክፉ ነገርንም ከቶ እንዳታደርጉ ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን፤ እኛ የምንበቃ ሆነን እንገለጥ ዘንድ አይደለም ነገር ግን እኛ ምንም እንደማንበቃ ብንሆን፥ እናንተ መልካሙን ታደርጉ ዘንድ ነው።“

/**ኤፌ** 1 ፥ 16/

“15 ስለዚህ እኔ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ስለሚሆን በጌታ በኢየሱስ ስለ ማመንና ለቅዱሳን ሁሉ ስለሚሆን መውደድ ሰምቼ፥

16 ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ስጸልይ ስለ እናንተ ማሳሰብን አልተውም፤

17 የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ።“

/**ቆላ** 1 ፥ 9/

“9 ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም።“

/1**ኛ ተሰ** 3 ፥ 10-11/

“9-10 ፊታችሁን ልናይ በእምነታችሁም የጎደለውን ልንሞላበት ሌሊትና ቀን ከመጠን ይልቅ እየጸለይን በአምላካችን ፊት ከእናንተ የተነሣ ስለምንደሰተው ደስታ ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ምን ያህል ምስጋና እናስረክብ ዘንድ እንችላለን? “

/**ፊል** 1 ፥ 3-5/

# ጸራቤ መናፍቃን (ዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ)

"3 ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

4-5 በጌታ በኢየሱስ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ ዘንድ ስላለህ ስለ ፍቅርህና ስለ እምነትህ ሰምቼ፥ በጸሎቴ እያሳሰብሁ ሁልጊዜ አምላኬን አመሰግናለሁ"

- ቅዱሳን አባቶቻችን ነቢያትም ሐዋርያትም በኅብረት ለሌሎች አማኞች ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን። እስከአሁን ድረስ እነርሱ ለሌሎች ሲጸልዩ ዐይተናል ፥ ነገር ግን ገና በዚህ አላበቁም። ይልቁንም ለተማሪዎቻቸው ለክርስቲያኖች ስለእኛ እና አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ ብለው አዘዋቸዋል። እስኪ ቅዱሳኑ ይህንን ሲሉ እንመልከት፥

/ሮሜ 15 ፥ 30/

"30 ወንድሞች ሆይ፥ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር እየጸለያችሁ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ፤"

/ኤፌ 6 ፥ 18/

"18 በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤ "

/1ኛ ጢሞ 2 ፥ 1 - 2/

"1-2 እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። "

/2ኛ ተሰ 3 ፥ 1 - 2/

"1-2 በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጌታ ቃል እንዲሮጥ በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን እንዲከበር፥ እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን ከዓመፀኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንድንድን ስለ እኛ ጸልዩ።"

/1ኛ ቆሮ 1 ፥ 10 - 11/

"10-11 እርሱም ይህን ከሚያህል ሞት አዳነን፥ ያድነንማል፤ እናንተም ደግሞ ስለ እኛ እየጸለያችሁ አብራችሁ ስትረዱን፥ በብዙ ሰዎች በኩል ስለ ተሰጠን ስለ ጸጋ ስጦታ ብዙዎች ስለ እኛ ያመሰግኑ ዘንድ፥ ወደ ፊት ደግሞ እንዲያድን በእርሱ ተስፋ አድርገናል።"

/ፊል 1 ፥ 19/

"19 ወደ ፊትም ደግሞ ደስ ይለኛል፤ ይህ በጸሎታችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት ለመዳኔ እንዲሆንልኝ አውቃለሁና።"

/1ኛ ተሰ 5 ፥ 25/

"25 ወንድሞች ሆይ፥ ስለ እኛ ጸልዩ።"

# ጸራቤ መናፍቃን (ዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ)

- እኒህ ቅዱሳን አባቶች ለሌሎች አማኞች ጸልዩ ሲሉ ራሳቸውም ደግሞ ለሌሎች ሲጸልዩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከጥግ እስከ ጥግ መመልከት እንችላለን። ነገር ግን ፥ እነርሱ ደግሞ ከየት እንደተማሩት እስኪ እንመልከት። የተማሩት ደግሞ ከክብር ባለቤት ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት እና ተግባር ነው። ይህንን ደግሞ እስኪ ከወንጌላቱ እንመልከት፥

/ማቴ 19 ፥ 13/

“13 በዚያን ጊዜ እጁን እንዲጭንባቸውና እንዲጸልይ ህፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም ገሠጹአቸው።

14 ነገር ግን ኢየሱስ፦ ህፃናትን ተዉአቸው፥ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና አለ።“

/ሉቃ 22 ፥ 32/

“31 ጌታም፦ ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤

32 እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ።“

/ዮሐ 17 ፥ 9/

“9 እኔ ስለ እነዚህ እለምናለሁ፤ ስለ ዓለም አልለምንም ስለ ሰጠኸኝ እንጂ፤ የአንተ ናቸውና፤

10 የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው የአንተውም የእኔ ነው፤ እኔም ስለ እነርሱ ከብሬአለሁ።“

- ስለዚህ እኒህ አባቶች ሐዋርያት በራሳቸው ያመጡት አይደለም ከክብር ባለቤት ከክርስቶስ የተማሩት ትምህርት ነው እንጂ። ስለዚህ ጠቅልለን አንድ አማኝ ለሌላ አማኝ መጸለይ እንደሚገባው አሳየን። መጽሐፍ ቅዱስ ውብ የኾነው የአምላካችን ቃል መኾኑን የምታዩት ለአማኞች ብቻ ጸልዩ ብሎ አያበቃም። ይልቁንም ገና ለማይወዷችሁም ጸልዩ ብሎ ያዘናልና። ይህንን ዐይተን ይህንን ክፍል አብቅተን ወደቀጣዩ ክፍል የምንገባ ይኾናል።

ከዓመፀኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንድንድን ስለ እኛ ጸልዩ።“

/ማቴ 5 ፥ 44-45/

“44-45 እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። “

/ሉቃ 6 ፥ 27 - 28/

“27 ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ፥ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ፥

28 የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ።“

## ፪. የቅዱሳን ጸሎት ደግሞ ለእግዚአብሔር በጣም ቅርብ ነው ፥ ስለዚህ የበለጠ ኀይል አለው።

ይህ ሐሳብ ምናልባት እምነታቸውን በደንብ ለማያውቁ ፕሮቴስታንቶች ባዕድ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ያነበበ ሰው ሊክደው የማይችል እውነት ነው። ይህንን ደግሞ አሁን ያለምንም ጥርጥር ከመጽሐፍ ቅዱስ እናረጋግጣለን። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ቅዱሳኑን እንደሚወዳቸው ይልቁንም ደግሞ እነርሱን ለመራዳት እጅግ ፈጣን እንደኾነ እንመልከት፥

/መዝ 1 ፥ 6/

“6 እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ ያውቃልና፥ የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች።“

/መዝ 14 ፥ 8 - 9/

“8 በዚያ በታላቅ ፍርሃት እጅግ ፈሩ፥ እግዚአብሔር በጻድቃን ትውልድ ዘንድ ነውና።

9 የድሆችን ምክር አሳፈራችሁ፥ እግዚአብሔር ግን ተስፋቸው ነው።“

/መዝ 34 ፥ 17 - 19/

“17 ጻድቃን ጮሁ፥ እግዚአብሔርም ሰማቸው ከመከራቸውም ሁሉ አዳናቸው።

18 እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፥ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል።

19 የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፥ እግዚአብሔርም ከሁሉ ያድናቸዋል።“

/መዝ 37 ፥ 16 - 18/

“16 ለጻድቅ ያለው ጥቂት ከብዙ ከኃጢአተኞች ሀብት ይበልጣል።

17 የኃጥአን ክንድ ትሰበራለችና፤ እግዚአብሔር ግን ጻድቃንን ይደግፋቸዋል።

18 የንጹሓንን መንገድ እግዚአብሔር ያውቃል፥ ርስታቸውም ለዘላለም ነው፤“

/መዝ 75 ፥ 9 - 10/

“9 እኔ ግን ለዘላለም ደስ ይለኛል፥ ለያዕቆብም አምላክ ዝማሬን አቀርባለሁ።

10 የኀጥኣንን ቀንዶች ሁሉ እሰብራለሁ፤ የጻድቃን ቀንዶች ግን ከፍ ከፍ ይላሉ።“

/ምሳ 3 ፥ 32 - 33/

“32 ጠማማ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ርኩስ ነውና፤ ወዳጅነቱ ግን ከቅኖች ጋር ነው።

33 የእግዚአብሔር መርገም በኃጥእ ቤት ነው፥ የጻድቃን ቤት ግን ይባረካል።“

/ምሳ 10 ፥ 30/

“30 ጻድቃን ለዘላለም አይናወጡም፤ ኀጥኣን ግን በምድር ላይ አይቀመጡም።“

/ሆሴ 14 ፥ 9/

“9 ይህን ነገር የሚያስተውል ጠቢብ፥ የሚያውቃትም አስተዋይ ማን ነው? የእግዚአብሔር መንገድ ቅን ነው፥ ጻድቃንም ይሄዱበታል፤ ተላላፊዎች ግን ይወድቁበታል።“

/ማቴ 13 ፥ 43/

“43 በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።“

/ማቴ 25 ፥ 46/

“46 እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ህይወት ይሄዳሉ።“

/ሮሜ 1 ፥ 7/

# ጸራቤ መናፍቃን (ዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ)

“7 በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።“

እግዚአብሔር ቅዱሳንን እንደሚወዳቸው በርግጠኝነት ተመልክተናል። ነገር ግን እግዚአብሔር ይህንን ብሎ አላበቃም ፥ እነርሱ የሚጸልዩት ጸሎት ከሌሎች ከኀጢአተኞች ጸሎት እጅግ የበረታ እንደኾነ። እግዚአብሔርም ወደእነርሱ ጸሎት በጣም ቅርብ እንደኾነ እንመለከታለን።

/ምሳ 15 ፥ 29/

“29 እግዚአብሔር ከኀጥኣን ይርቃል፤ የጻድቃንን ጸሎት ግን ይሰማል።“

/መዝ 34 ፥ 15/

“15 የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸውና። “

/1ኛ ጴጥ 3 ፥ 12/

“12 የጌታ ዓይኖች ወደ ጻድቃን ናቸውና፥ ጆሮዎቹም ለጸሎታቸው ተከፍተዋል፥ የጌታ ፊት ግን ክፉ ነገርን በሚያደርጉ ላይ ነው።“

/ያዕ 5 ፥ 16/

“15 የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል።

16 እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።“

/ራእ 8 ፥ 4/

“2 በእግዚአብሔርም ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ፥ ሰባትም መለከት ተሰጣቸው።

3 ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሰዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሰዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው።

4 የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ።“

“እግዚአብሔር የቅዱሳንን ጸሎት ይሰማል ፥ ይልቁንም ለእነርሱ በጣም ቅርብ ነው።“ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ያስተምራል። እንዲሁ ደግሞ ብሎ አያበቃም ፥ ነገሩ ገና እጅግ ውብ እየኾነ ይመጣል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አስተምህሮ በህይወታቸው የተገበሩ ሰዎችንም ደግሞ ይገልጥልናል። እንዲያውም እግዚአብሔር ራሱ ‘ ይህ ቅዱስ ቢያማልድህ እምርሃለሁኝ’ ብሎ ሲናገር እንመለከታለን፥

/ዘፍ 18 ፥ 22 - 33/

“22 ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ፥ ወደ ሰዶምም ሄዱ፤ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር።

23 አብርሃምም ቀረበ አለም፦ በውኑ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ታጠፋለህን?

24 አምሳ ጻድቃን በከተማይቱ ውስጥ ቢገኙ በውኑ ሁሉን ታጠፋለህን? ከተማይቱንስ በእርስዋ ስለሚገኙ አምሳ ጻድቃን አትምርምን?

25 ይህ ከአንተ ይራቅ፤ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ትገድል ዘንድ፥ ጻድቁም እንደ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ፥ እንደዚህ ያለው አድራጎት ከአንተ ይራቅ። የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?

26 እግዚአብሔርም፦ በሰዶም በከተማይቱ ውስጥ አምሳ ጻድቃን ባገኝ ስፍራውን ሁሉ ስለ እነርሱ እምራለሁ አለ።

27 አብርሃምም መለሰ አለም፦ እኔ አፈርና አመድ ስሆን ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ እነሆ አንድ ጊዜ ጀመርሁ፤

28 ከአምሳው ጻድቃን አምስት ቢጐድሉ ከተማይቱን ሁሉ በአምስቱ ምክንያት ታጠፋለህን? ከዚያ አርባ አምስት ባገኝ አላጠፋትም አለ።

29 ደግሞም ተናገረው፥ እንዲህም አለ፦ምናልባት ከዚያ አርባ ቢገኙሳ? እርሱም፦ ለአርባው ስል አላደርገውም አለ።

30 እርሱም፦ ጌታዬ አይቆጣ እኔም እናገራለሁ፤ ምናልባት ከዚያ ሠላሳ ቢገኙሳ? አለ። እርሱም፦ ከዚያ ሠላሳ ባገኝ አላጠፋም አለ።

31 ደግሞም፦ እነሆ፥ ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ አንድ ጊዜ ጀመርሁ፤ ምናልባት ከዚያ ሀያ ቢገኙሳ? አለ። እርሱም፦ ከዚያ ሀያ ቢገኙ ስለ ሀያው አላደርገውም አለ።

32 እርሱም፦ እኔ ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ ብናገር ጌታዬ አይቆጣ፤ ምናልባት ከዚያ አሥር ቢገኙሳ? አለ። እርሱም፦ ስለ አሥሩ አላጠፋትም አለ።

33 እግዚአብሔርም ከአብርሃም ጋር ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ሄደ፤ አብርሃምም ወደ ስፍራው ተመለሰ።“

/ዘፍ 20 ፥ 6 - 17/

“6 እግዚአብሔርም በህልም አለው፦ ይህን በልብህ ቅንነት እንዳደረግህ እኔ አወቅሁ፥ እኔም ደግሞ በፊቴ ኃጢአትን እንዳትሠራ ከለከልሁህ፤ ስለዚህም ትነካት ዘንድ አልተውሁም።

7 አሁንም የሰውዬውን ሚስት መልስ ነቢይ ነውና፥ ስለ አንተም ይጸልያል፥ ትድናለህም። ባትመልሳት ግን አንተ እንድትሞት ለአንተ የሆነውም ሁሉ እንዲሞት በእርግጥ እወቅ።

. . .

17 አብርሃምም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም አቢሜሌክን ሚስቱንም ባሪያዎቹንም ፈወሳቸው፥ እነርሱም ወለዱ።“

/ኢዮ 42 ፥ 7 - 10/

“7 እግዚአብሔርም ይህን ቃል ለኢዮብ ከተናገረ በኋላ እግዚአብሔር ቴማናዊውን ኤልፋዝን፦ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቍጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዶአል።

8 አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎች ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ዘንድ ሂዱ፥ የሚቃጠልንም መሥዋዕት ስለ ራሳችሁ አሳርጉ፤ ባሪያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፥ እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ፤ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና።

9 ቴማናዊውም ኤልፋዝ ሹሐዊውም በልዳዶስ ናዕማታዊውም ሶፋር ሄደው እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ፤ እግዚአብሔርም የኢዮብን ፊት ተቀበለ።

10 ኢዮብም ስለ ወዳጆቹ በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔርም ምርኮውን መለሰለት፤ እግዚአብሔርም ቀድሞ በነበረው ፋንታ ሁለት እጥፍ አድርጎ ለኢዮብ ሰጠው።“

**/ዘጸ** 32 ፥ 10 - 14/

“10 አሁንም ቍጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ፤ አንተንም ለታላቅ ህዝብ አደርግሃለሁ አለው።

11 ሙሴም በእግዚአብሔር በአምላኩ ፊት ጸለየ፥ አለም፦ አቤቱ፥ ቍጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብፅ ምድር ባወጣኸው በህዝብህ ላይ ስለ ምን ተቃጠለ?

12 ግብፃውያንስ፦ በተራራ መካከል ሊገድላቸው፥ ከምድርም ፊት ሊያጠፋቸው ለክፋት አወጣቸው ብለው ስለ ምን ይናገራሉ? ከመዓትህ ተመለስ፥ ለህዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ።

13 ዘራችሁን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ፥ ይህችንም የተናገርኋትን ምድር ሁሉ ለዘራችሁ እሰጣታለሁ፥ ለዘላለምም ይወርሱአታል ብለህ በራስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይስሐቅን እስራኤልንም አስብ።

14 እግዚአብሔርም በህዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ።“

**/መዝ** 106 ፥ 23/

“23 እንዳያጠፋቸው ቍጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ፥ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ።“

ነገራችንን ስንጠቀልል ያለምንም ጥርጥር መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሳን ጸሎት ኀያል እንደኾነ ፥ ታላላቅ ድንቆችንም ማድረግ እንደሚችል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ይህንን ከጠነቀቅን ደግሞ ‘ቅዱሳን በገነት ውስጥ ንጹሐን ፥ ከኀጢአት የነጹ ኾነው ይኖራሉ።’ የሚለውን ደግሞ ፈጥነን እንመልከት።

## ፫. ቅዱሳን ካረፉ በኋላ በገነት ውስጥ ንጹሐን፤ ከኀጢአት የተላቀቁ ይኾናሉ።

እስከአሁን ያየናቸው ፥ አሁንም የምናየውን ጨምሮ የሚያጣላ አይደለም። የሚያጣላው ከ4ኛ ጀምሮ ያሉት ናቸው። እስከዚህ ድረስ ግን የመጣነው እንደእግዚአብሔር ፈቃድ በተቻለ የተጠናቀቀ አሳማኝ ማስረጃ ለማቅረብ ነው። ይህን ካልን ፥ ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ በገነት ውስጥ በክብር እንደሚኖሩ ከዚህ በኋላ እናሳያለን።

**/2ኛ ጢሞ** 4 ፥ 7 - 8/

“7 መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤

8 ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።“

**/ዕን 1 ፥ 13/**

“13 ዓይኖችህ ክፉ እንዳያዩ ንጹሐን ናቸው፥ ጠማምነትንም ትመለከት ዘንድ አትችልም፤ አታላዮችንስ ለምን ትመለከታለህ? ኃጢአተኛውስ ከእርሱ ይልቅ ጻድቅ የሆነውን ሲውጠው ስለ ምን ዝም ትላለህ?“

**/ዕን 1 ፥ 13/**

“2 ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።“

- ከ2ኛ ጢሞ 4 ፥ 7 – 8 እንደምንረዳው ከሞት በኋላ ወደ ገነት መግባት ለደጋጎች ሁሉ የመጨረሻ የእግዚአብሔር ሽልማት ነው። ያን ጊዜ የምንኖረው በደስታ ከጌታችን ጋር ይኾናል። እርሱንም ‘እንዳለ’ እናየዋለን። ነገር ግን አንድ ነገር እንጠይቅ ፥ ‘በሰማይ ጌታችንን እንደምልዐቱ እስከነኀጢአታችን ማየት እንችላለን? ከጌታችን ፊት እየኖርን ኀጢአት ሊፈታተነን ይችላል?’ የሚለው ነው። መልሱም ‘ሊኾን አይችልም’ ነው። ምክንያቱ ደግሞ በዕብባቆም ትንቢት ያለው ቃል ነው። ‘ዐይኖችህ ክፉ እንዳያዩ ንጹሓን ናቸው።’ ሲል እግዚአብሔር በሰማይ በምልዐቱ ለቅዱሳኑ በሚገለጥበት ቦታ ላይ እነርሱ ፍጹማን ንጹሓን መኾን ስላለባቸው ነው።

**/ዕብ 11 ፥ 39 - 40/**

“39-40 እነዚህም ሁሉ በእምነታቸው ተመስክሮላቸው ሳሉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም፥ ያለ እኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ እግዚአብሔር ስለ እኛ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቀድሞ አይቶ ነበርና።“

**/ዕብ 12 ፥ 23/**

“23 በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች።“

- ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሁለት ነገርን ያረጋግጥልናል። ይህም በመጀመሪያ በሰማይ ያሉ የቅዱሳን ነፍሳት ጽጹማን እንደኾኑ /ዕብ 12 ፥ 23/ ፥ ነገር ግን ገና ሌሎች ኋላ የሚመጡ ነፍሳት አሉና ነፍሳቱ ምንም ፍጹማን ከኀጢአት የነጹ ቢሆን የፍጻሜውን የተስፋ ቃል እንዳልተቀበሉ ነው/ዕብ 11 ፥ 39 – 40/። ስለዚህ በእነዚህ ቃላት ሁለት ቦታዎች ማለትም ገነት እና ኢየሩሳሌም ሰማያዊት የሚባሉ እንዳሉ ፥ ይልቁንም ገነት ማረፊያ እንደኾነች። ዘመን ሲደርስ ደግሞ የተስፋ ቃል ወደተባለችው ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ነፍሳት ሁሉ እንደሚገቡ እንመለከታለን።

**/ራእ 7 ፥ 13 - 17/**

“13 ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ፦ እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አለኝ።

14 እኔም፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ታውቃለህ አልሁት። አለኝም፦ እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ።

15 ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፥ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።

16 ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፥ ከእንግዲህም ወዲህ አይጠሙም፥ ፀሐይም ትኲሳትም ሁሉ ከቶ አይወርድባቸውም፤

17 በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፥ ወደ ህይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።"

- ቅዱሳኑ ከሞት በኋላ ቀድሞ ከነበሩበት ህይወት በላይ በንጽህና በፍጽምና እንደሚኖሩ ይህ ቃል ግልጥ ማስረጃ ነው። ከዚህ በኋላ ሥቃይ የለባቸውም፣ ፈተና የለባቸውም፣ አይራቡም አይጠሙም። በበጉ ደም ልብሳቸውን ራሳቸውን አጥበዋልና። ከዚህ በኋላ ፈተና እና ድካም አያገኛቸውም። ጌታ ሆይ ፥ ለዚህ ክብር አብቃን። እስከፍጻሜያችን እንታገላለን ፥ አንተ ደግሞ አብረኸን ቀንበሩን እንደምትሸከምልን እናምናለን። አቤቱ ሆይ ፥ ከአንተ ፍቅር ተለይተን አንኑር። ለዚህ ክብር አብቃን።

ከዚያም ደግሞ እንደማጠቃለያ ማስረጃ የምናቀርበው የሰው ልጅ በጌታችን ሞትና ትንሣኤ ወደቀድሞ ቦታው መመለሱን ነው። ቀድሞ እግዚአብሔር አዳምን ያባረረው በኀጢአት ምክንያት ከኾነ እንዴት በገነት በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ኀጢአትን ሊፈቅድ ይችላል? ሊኾን የማይችል ነገር ነው። የሰው ልጅ ዘለዓለማዊ ሲኾን በምድር የሠራው ደግ ከኾነ ለዘለዓለም በደስታ ያለምንም የኀጢአት መፈታተን እንደሚኖር በዚህ እናውቃለን። ከዚህ በመቀጠል ዋነኞቹ የክርክር ሁሉ መንሥኤ የኾኑትን ሁለት ማስረጃዎች እናረጋግጥ።

፫. ቅዱሳን በሰማይ በገነት ህያዋን ናቸው። (የሞቱ አይደሉም)

ከዚህ በኋላ ነው ዋነኛው ጦርነት የሚጀምረው ፥ ፕሮቴስታንቶችም ከሥራቸው የኾነ ነገር እነርሱን መቆንጠጥ የሚጀምረው ከዚህ ጀምሮ ነው። እስከአሁን ያለውን ነገር ለአንድ ፕሮቴስታንት ካሳዩ በኋላ ማለት የሚችሉት አንድ እና አንድ ገር ብቻ ይኾናል። "ወደሞቱ ሰዎች ትጸልያላችሁ" የሚል ይኾናል። ከዚያ ይህንን ስንረታቸው ደግሞ የመጨረሻ መንጠልጠያ ግንድ ደግሞ "ሰማይ ላይ ህያው ናቸው ነገር ግን በምድር ላይ የሚኾነውን ነገር አያውቁም" የሚል ይኾናል። ኋለኛውን በመጨረሻው የማስረጃ ክፍል የምንደርስበት ሲኾን ለአሁን ግን ቅዱሳን በሰማይ በገነት ውስጥ ህያዋን እንጂ የሞቱ እንዳልኾኑ ፥ ይልቁንም ቦታ ቀየሩ እንጂ የበለጠ ህያዋን መኾናቸውን እንመለከታለን።

ይህንን ማሳየጥ ከቻልን ብዙ ነገሮች ተከታትለው ይመጣሉ። ቅዱሳን ገነት ውስጥ ሲገቡ ከኀጢአት የነጹ ስለሚኾኑ ጸሎታቸው የበለጠ ብርቱ ይኾናል። ቀድሞን እንዳየነው ደግሞ ከዚህ በኋላ የሚፈታተናቸው ኀጢአት ስለሌለ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በፍጽምና መፈጸም ይችላሉ። መጀመሪያ ስናየው እንደነበረው እግዚአብሔር ካዘዛቸው ትእዛዛት መካከል ደግሞ ለደካማው ወንድምና እኅት መጸለይ ነው። ስለዚህ በምድር ያደረጉት ከነበረው በገነት ውስጥ የበለጠ ቅድስና የሚሠሩ ከኾነ ፥ በምድር ይጸልዩ ከነበረው በላይ በሰማይ መጸለይ ይችላሉ ማለት ነው። ስለዚህ የቅዱሳንን ምልጃ ለማረጋገጥ ጫፍ ደረስን ማለት ነው። ስለዚህ ወደ ማረጋገጡ እንሂድ፥

/መዝ 69 ፥ 28/

"28 ከህያዋን መጽሐፍ ይደምሰሱ፥ ከጻድቃንም ጋር አይጻፉ።"

/መዝ 115 ፥ 18/

"18 እኛ ህያዋን ግን ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔርን እንባርካለን። ሃሌ ሉያ።"

- ፕሮቴስታንቶች አሁን ጠባቸው ከእኛ ጋር ሳይኾና ከቅዱስ ዳዊት ጋር ነው። ቅዱስ ዳዊት 'እኛ ህያዋን ነን' እያለ ሲጠራ እናንተ ደግሞ 'አይ ፥ አንተ የሞትህ ነህ' ትሉታላችሁ። ማናችሁን መስማት ይሻለናል ፥ ወንድሞቼ እና እኅቶቼ ሆይ እኔ ቅዱስ ዳዊትን መርጫለሁኝ። እናንተ ደግሞ የምትወዱትን ምረጡ። እርሱ ተሳሳተ ልትሉ ነው? እርሱን ካላችሁት ቀጥታ ማንን እንደሰደባችሁ እስኪ እንመልከት፥

# ጸራቤ መናፍቃን (ዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ)

/ማቴ 22 ፥ 31 - 32/ማር 12 ፥ 27/ሉቃ 20 ፥ 38/

“31-32 ስለ ትንሣኤ ሙታን ግን፦ እኔ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን? የህያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም። “

- አስተዋላችሁ መሰለኝ ማንን ተሳሳተ እንዳልችሁ። እግዚአብሔር ‘የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ እምላክ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ፥ ብሎ የህያዋን አምላክ ነኝ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለሁም።’ አለ። ስለዚህ እናንተ ማን ናችሁና ነው ቅዱሳእነ የሞቱ ናቸው የምትሉት? ሞት ማለት ቦታ መቀየር ከኾነ ከየት ነው ያመጣችሁን ይህንን ግራ የተጋባ የሞት ትርጉም? ሞት ማለት መሸጋገሪያ ማለት ነው እንጂ ሙሉ ለሙሉ መጥፋት ማለት አይደለም። ስለዚህ ክርስቶስ ‘ህያዋን ናቸው በሉ።’ እያለ ‘የሞቱ ናቸው’ ስትሉ ጠባችሁ ከእኙዓ ጋር አይደለም። ከክብር ባለቤት ከክርስቶስ ጋር ነው። ‘መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ’ ትሉ የለ? ይኸው መጽሐፍ ቅዱስ አቀረብንላችሁ ፥ በሉ ተቀበሉት።
- ምናልባት አይ ‘ህያዋን’ የሚላቸው ከኀጢአት ስለነጹ ነው ትሉ ይሆናል። ነገር ግን ይህቺ ማምለጫ አሁን አትሠራም። በመጀመሪያ ጌታችን በሥጋ በነፍስ እያለ ፈጽሞ አልለየም። ሙታን እላችሁ አትጥሯቸው አለ እንጂ። ሁለተኛ ደግሞ ‘ሞት’ ከሚለው ቃል ውስጥ የትኛው ክፍል ነው ያልገባችሁ ‘ሞ’ የሚለው ነው ወይስ ‘ት’ የሚለው ክፍል? ሞት ማለት በህይወት እንዳሉ ሽግግር ማለት ነው እንጂ ከግኝት መጥፋት ማለት አይደለም። ስለዚህ እንዲህ ብላችሁ ማምለጥ አትችሉም። እውነታውን ተገፈጡ። ቅዱሳን በሰማይ ላይ ህያዋን ናቸው እንጂ ሙታን ተብለው አይጠሩም። ይህንን ሐሳብ መጠቅለል ከቻልን ወደ መጨረሻው ማስረጃ እንሄዳለን። ቅዱሳን በእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር የሚከናወነውን ያውቃሉ ፥ ይህንን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማሳየጥ ከቻልን ፕሮቴስታንቲዝም አበቃለት። አሁንም ኦርቶዶክስ ልክ ናት ማለት ነው። እኛ ደግሞ ይህንን ለማሳየት ከደስተኞችም በላይ ስለኾንን እንቀጥል።

## ፭. <u>እግዚአብሔር ለቅዱሳን በምድር የሚከናወነውን እንዲያውቁ አድርጓቸዋል።</u>

/ሉቃ 15 ፥ 7/

“7 እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ <u>ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል</u>።“

- ጌታችን ቃል በቃል ተናገረ ፥ አንድ ሰው በምድር ሲኖር ንስሐ ሲገባ በሰማይ ታላቅ ደስታ ይኾናል። ነገር ግን በሰማይ ያሉት እንዲደሰቱ መጀመሪያ አንድ ሰው በኀጢአት ይኖር እንደነበረ፣ ከዚያ ደግሞ ተጸጽቶ ወደ ንስሐ እንደገባ ማወቅ የለባቸውም? ያውቃሉ ማለት ነው። ደግሞ በዓለም ውስጥ ያሉትን ንስሐ የሚገቡትን ሰዎች በሙሉ የማወቅ ኀይል ሊኖራቸው ይገባል። እግዚአብሔር አሳውቋቸዋል ማለት ነው።

/ሉቃ 16 ፥ 24 - 29/

“24 እርሱም እየጮኸ፦ አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ።

25 አብርሃም ግን፦ ልጄ ሆይ፥ አንተ በህይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ።

26 ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።

27 እርሱም፦ እንኪያስ፥ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤

28 እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ።

29 አብርሃም ግን፦ ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው።"

- አስተውሉ አብርሃም ከሞተ ከብዙ ዘመናት በኋላ የሚከናወንን ታሪክ ነው ጌታችን እንደምሳሌ አድርጎ የሚገልጽላቸው። ነዌ ለአብርሃም አልአዛርን ውኃ እንዲያጠጣው እንዲልክለት ሲጠይቀው አብርሃም የመለሰለት መልስ ነው እዚህ ጋር ቁልፋችን። አብርሃምም 'ልጄ ሆይ፥ አንተ በህይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ።' አለው። አብርሃም ለነዌ በምድር ሳለ የኖረውን አኗኗር ነው የገለጸለት። ፕሮቴስታንቶች እንደሚሉት አብርሃም በምድር የሚኾነውን የማያውቅ ቢኾን እንዴት ነው የነዌንና የአልአዛርን ኑሮ እንዲህ አድርጎ ሊያውቅ የሚችለው። ፕሮቴስታንቶች አትልፉ ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ፕሮቴስታንታዊ መጽሐፍ አይደለም ፥ ኦርቶዶክሳዊ እንጂ።

/ራእ 5 ፥ 8/

"8 መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ፥ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ።"

/ራእ 8 ፥ 3 - 4/

"3 ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሰዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሰዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው።

4 የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ።"

- አብዛኛው ጊዜ በጣም ከምንሰማቸው የፕሮቴስታንት ወቀሣዎች መካከል አንዱ 'ኦርቶዶክሶች ቀጥታ ወደክርስቶስ አይሄዱም ፥ በዙሪያ መሄድ ይወዳሉ።' የሚል ነው። ይኽ ጥቀስ ግን ይኽንንም አስተሳሰብ ይቀብረዋል። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊው ሆይ እንዴት እንደዚኽ ትላለህ? የቅዱሳን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር የሚደርሰው በቅዱሳን መላእክት በኩል ነው? የሚያሳዝን ነው ፥ እንደፕሮቴስታንቶቹ ባዶ ፍልስፍና መሠረት እግዚአብሔር ራሱ በዙሪያ መሄድ ይወዳል ማለት ነው። የቅዱሳንን ጸሎት ቀጥታ መስማት እየቻለ ለምንድን ነው እግዚአብሔር በመላእክት ማጠኛ እንዲያርግ የሚያደርገው? እግዚአብሔር ራሱ በቀጥታ መሄድ አይችልም ፥ በዙሪያ ነው መሄድ የሚወደው ማለት ነው። አኹን ታያችሁ የእነዚህ ፍልስፍና የት እንደሚደርስ? ቅዱስ ጳውሎስ 'ባዶ ፍልስፍና' ያለው ይኽን ዐይነቱን ነው። /ቆላ 2 ፥ 8/
- በተጨማሪም ደግሞ መላእክቱ በምድር የሚኾነውን እንደሚያውቁ ከዚኽ ጥቅስ እንረዳለን። አንደኛ ከዓለም ኹሉ ያሉትን ጻድቃን ጸሎት እንዲያሳርጉ እግዚአብሔር ለመላእክቱ እጅግ ድንቅ የኾነ ኀይል እንደሚሰጣቸው ፥ ደግሞም የትኛው ጻድቅ እየጸለየ እንደኾነ እንዲያውቁ ደግሞ ዕውቀትን እንደሰጣቸው ይኽ ጥቅስ ያሳየናል።

/ራእ 6 ፥ 9 - 11/

"9 አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ።

10 በታላቅ ድምፅም እየጮሁ፦ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ።

11 ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፥ እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ፥ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው።"

- በጣም ነው የሚገርመው ፥ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ፕሮቴስታንት ፕሮቴስታንት አይሸትም። ኦርቶዶክስ ኦርቶዶክስ ነው የሚሸተው። ቅዱስ ዮሐንስ ያየው በሰማዕትነት ያረፉ ነፍሳትን ነው ፥ ማለትም ያሉት በገነት ውስጥ ነው። ካስተዋላችሁ ቅዱስ ዮሐንስ የፕሮቴስታንት እምነትን ደምስሶታል። በሰማይ ያሉት ቅዱሳን ለእግዚአብሔር 'አትፈርድልንምን?

ደማችንን አትበቀልምን።' አሉት። ቆይ ቆይ ፕሮቴስታንቶች ፣ ቅዱሳኑ በምድር ላይ የሚኾነውን የማያውቁ ከኾነ ይፈረድላቸው አይፈረድላቸው ፣ እግዚአብሔር በምድር እንደተበቀለላቸው እንዳልተበቀለላቸው በምን ዐወቁ? አሁን መብራቱ ብልጭ አለ ፣ መሰለኝ። ቅዱሳኑ በምድር ያለውን ባያውቁ ኖሮ ፣ በምድር እግዚአብሔር ደማቸውን ይበቀል አይበቀል ስለማያውቁ 'ለምን እስከአሁን አልተበቀልክልንም?' ብለው መጠየቅ አይችሉም ነበር። ቅዱሳኑ በምድር ላይ የሚከናወነውን ቢያውቁ ነው ማለት ነው።

- ገና አላበቃንም ፣ ከዚያ ቀጥሎ እግዚአብሔር ያላቸውን ተመልከቱ። 'እንደእነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልእንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ' ብሎ ነጭ ልብስን ሰጣቸው። አስተውሉ ፣ እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ ቀጥታ በምድር ላይ የሚኾነውን እኮ ነው የነገራቸው ፣ ገና ሰማዕታቱ ይሞታሉ። ገና ቅዱሳኑ እናንተን ይሚቀላቀሉ አሉ ብሎ በምድር ላይ ስላሉ ቅዱሳን ነው የነገራቸው እኮ። በአንድ ጥቅስ ሁለት ጊዜ ቅዱሳን በምድር ላይ የሚኾነውን ማወቅ እንደሚችሉ ተመለከትን።

/ራእ 18፥20/

"20 <u>ሰማይ ሆይ፥ ቅዱሳን ሐዋርያት ነቢያትም ሆይ፥ በእርስዋ ላይ ደስ ይበላችሁ፥</u> እግዚአብሔር ፈርዶላችኋልና።"

- ይኽ ቃል ማኅተማችን ይኾናል። ቅዱሳን ሆይ ደስ ይበላችሁ ፣ ሐዋርያትና ነቢያትም ሆይ ደስ ይበላችሁ ፣ እግዚአብሐየር ፈርዶላችኋልና። ቀጥታ ለሐዋርያትና ለነቢያት እግዚአብሔር በምድር ለእነርሱ እንደተበቀለላቸው ፣ የተንገላቱትን መንገላታት እግዚአብሔር እንደከፈላቸው ተነገራቸው። ታዲያ ይኽ ኹሉ ማስረጃ እያለ 'በሰማይ ያሉ ቅዱሳን በምድር ያለውን ትምህርት አያውቁም።' የሚለውን ፍልስፍና ከየት እንዳመጡት አናውቅም።

ነገራችንን በእግዚአብሔር ፈቃድ በቅዱሳን አማላጅነት ፈጸምን። መጀመሪያ ያነሣናቸውን ነጥቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ አረጋገጥን። እናስታውሳቸው፥

1) አንድ ክርስቲያን ለሌላ ክርስቲያን እንዲጸልይ ታዟል።

2) የቅዱሳን ጸሎት ደግሞ ለእግዚአብሔር በጣም ቅርብ ነው ፣ ስለዚኽ የበለጠ ኀይል አለው።

3) ቅዱሳን ካረፉ በኋላ በገነት ውስጥ ንጹሓን፣ ከኀጢአት የተላቀቁ ይኾናሉ።

4) ቅዱሳን በሰማይ በገነት ሕያዋን ናቸው። (የሞቱ አይደሉም)

5) እግዚአብሔር ለቅዱሳን በምድር የሚከናወነውን እንዲያውቁ አድርጓቸዋል።

እኒኽ ነገሮች እውነት ከኾነ (እውነት እንደኾኑም አሳይተናል) ያን ጊዜ ቅዱሳኑን በሰማይ ሳሉ ጸልዩልን ማለት እንችላለን ማለት ነው። እነርሱ ጋር ደግሞ የምንጸልየው ከእኛ በጣም በብዙ ስለሚበልጡን ነው ፣ በሰማይ ፍጹማን እንደኾኑ ዐይተናል። ስለዚኽ ለቅዱሳኑ መጸለይን ከመጽሐፍ ቅዱስ አረጋገጥን ፣ አኹንም ድጋሚ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልክ እንደኾነች መጽሐፍ ቅዱስ መሰከረ። ፕሮቴስታንቶች መታገሉን ተዉ ፣ እናታችሁ ትጠብቃችኋለች። ቤተክርስቲያናችሁ ትጠብቃችኋለች።

እመቤታችን የሰማይ ንግሥት፣ የደናግል መመኪያ፣ የአምላክ እናት፣ የሰማዕታት አክሊል፣ ዳግማዊት ሰማይ ሆይ ጸልዩልን። ቅዱሳን መላእክት ሆይ ጸልዩልን፣ ቅዱሳን ሐዋርያት ሆይ ጸልዩልን፣ ማኅቶተ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ሆይ ጸልይልን፣ ቅዱሳን ነቢያት ሆይ ጸልዩልን፣ ቅዱሳን መሳፍንት ሆይ ጸልዩልን፣ ቅዱሳን ነገሥታት ሆይ ጸልዩልን፣ ቅዱሳን አባቶች አግናጥዮስ ሆይ፣ ፖሊካርፕ ሆይ፣ ፓፒየስ ሆይ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ ሆይ፣ ቅዱስ ሄሬኔዎስ ሆይ፣ ቅዱስ ቀለሜንጦስ ሆይ፣ የመናፍቃን መዶሻ ቅዱስ ቄርሎስ ሆይ፣ ቅዱስ ሰቨረስ ሆይ፣ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ሆይ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሆይ፣ ሊቃውንት ሆይ ለምኑንልን ፣ ጸልዩልን። ቅዱሳን አባቶቻችን እናቶቻችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሆይ፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ አቡነ አረጋዊ፣ እናታችን ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ፣ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ሆይ ጸልዩልን ፣ ለምኑልን። በሰማይ ያለሽው ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ሆይ በምድር ላለን ጸልዩልን።

## ጸራቤ መናፍቃን (ዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ)

አስጀምሮ ላስፈጸመ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር እና ምሥጋና ይኹን። ክርስቶስ ተነሥቷል በእውነት ተነሥቷል

ኪርያላይሶን እግዚአብሔር አብ ሆይ ማረን ፥ ኪርያላይሶን እግዚአብሔር ወልድ ሆይ ማረን ፥ ኪርያላይሶን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሆይ ማረን። ማራናታ ፥ ጌታ ሆይ አትዘግይ ቶሎ ና።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር ለዓለመ ዓለም አሜን